**FEDERATION OF AMHARAS IN NORTH AMERICA (FANA)**
fanalightofamhara@gmail.com

**05/02/2024** **Ref # FANA_2024_00132**

# ከዐማራ ማህበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ (ፋና) የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ

**" አንድ ሁኑ! " ብርጋዴር ጀነራል አሳምነው ፅጌ**

ላለፉት ብዙ አስርት ዓመታት ጀምሮ የዐማራ ሕዝብ ከዚህ ምድር እንዲጠፋ ፀረ-አማራ ሃይሎች ፀረ-አማራ የሃሰት ትርክቶችን ወደ ሰነድ በመቀየር ስልታዊና መንግስታዊ በሆነ አወቃቀር የህልውና አደጋ ጋርጠውበታል። አፓርታይድአዊው የአብይ አህመድ አገዛዝ ከመጣ ወዲህ ደግሞ በአስቸኳ ጊዜ አዋጅ ስም፤ በዐማራው ላይ በግልፅ በጠራራ ፀሐይ ጦር አዝምቶ በአየር፣በድሮን፣ በታንክ፣ በመድፍ፣ ወዘተ በመጠቀም የዘር ማጥፋት ዘመቻው በፍጥነት እየከወነ ይገኛል። ይህን በመረዳት አማራ እንደ ህዝብ ቀድሞ ራሱን ባለማደራጀቱ እንደ ህዝብ ብዙ ዋጋ ከፍሏል እየከፈለም ይገኛል።

አፓርታይድአዊው የአብይ አህመድ አገዛዝ አማራን በአንድ ጀምበር በታትኖ ለማጥፋት ከመቸኮሉ የተነሳ የቀድሞውን የአማራ ልዩ ኃይልን በመበተን በአማራ ላይ ጦር አዝምቶ ጭፍጨፋውን ከጀመረ አንድ ዓመት ሞላው። ሳይደግስ አይጣላምና ይህ የተበተነ ኃይል እነሱ እንዳሰቡት ሳይሆን ቀድሞም በመደራጀት ላይ የነበረውን የፋኖ አደረጃጀት የጀርባ አጥንት በመሆን እጅጉን አፋጠነው።

የፋኖ አደረጃጀትና ፍጥነት፣ ወታደራዊ ዲስፕሊንና ብስለት፣ ጀግንነትና የሞራል ከፍታ ድፍን ዓለምን አስደምሟል። በርካታ የአለም አቀፍ ሚዲያዎች ሳይቀሩ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ይህን ፈጣን አደረጃጀት ታሪክ ሲዘክረው ይኖራል።
ሆኖም ግን አማራ ካለበት ስጋት አንፃር፣ የብልፅግና መንግስት በጥላቻ ስካር በአማራ ላይ ካወጀው ፍጅት አንፃር፣ ፋኖ አሁንም ከዚህ በፈጠነና በጠነከረ አደረጃጀት ወደ አንድነት መምጣት አለበት ብለን እናምናለን።

ቀደም ብሎ አደረጃጀቱን የጨረሰው የአማራ ፋኖ በጎጃም ለጠቅላላው አደረጃጀት ሂደት ወሳኝና ፋና ወጊ በመሆን ታሪክ ሲያስታውሰውና ሲዘክረው ይኖራል። በቅርቡ በጎንደር ጠቅላይ ግዛትና በወሎ ጠቅላይ ግዛት ያሉት የፋኖ አደረጃጀቶች ወደ አንድ ወጥ አደረጃጀት መምጣት በውስጥም በውጭም ለሚገኘው አማራና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ከፍተኛ ደስታን ከመፍጠሩ ባሻገር ለትግሉ ከፍተኛ መነቃቃትና አንድነት እንደሚፈጥር ግልፅ ነው። በቀጣይም በሸዋ ጠቅላይ ግዛት የተጀመረው ወጥ የሆነ አደረጃጀት ጨርሶ በቅርብ እንደሚያሳውቅ ጥርጥር የለንም።

በመሆኑም አንድ ወጥ የሆነ የአማራ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ኃይል ምስረታ መሬት ላይ በቅርቡ እውን እንደሚሆን የታወቀ ነገር ነው። “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር” እንዲሉ ለዚህም አንድ ወጥ የሆነ የአማራ አደረጃጀት የአራቱም ጠቅላይ ግዛቶች እያንዳዳቸው ወደ አንድ የፋኖ አደረጃጀት መምጣት ፋና ወጊ እንቅስቃ ነው።

የአማራ ፋኖ አንድ ሲሆን የአማራ ህዝብ አንድ ይሆናል፣ የውጭ ደጋፊወቻችሁ አንድ እንሆናለን፣ የውጭ ዲፕሎማሲ ማህበረሰብና መንግስታት ማነን እንደሚያናግሩ ያውቃሉ፣ ከፋፋዮቻችሁ ተስፋ ይቆርጣሉ፣ ጠላቶቻችን ይርዳሉ ፤ ይፍረከረካሉ፤ ይፈራርሳሉ።

በመጨረሻም የአማራ ሕዝብ የተደቀነበትን የህልውና አደጋ ተገንዝቦ ከዚህ በበለጠ ስልት እና ጥበብ በተሞላበት መንገድ ተደራጅቶ ፣ ሴራውን ማምከን፣ ካሳለፍነው ተመክሮቻችን ትምህርት በመውሰድ፤ የምንሞተው እንደ አማራ መሆኑን ተገንዘበን በሁሉም አቅጣጫ እንደ አማራ ተደራጀትን የተደቀነብንን የዘር ማጥፋትና ጭፍጨፋ ባልዘነጋ መልኩ በቁጭት፣ በንዴት እና በእልህ እንድነታችን አጠናክረን እንድንቀጥል ወገናዊ ጥሪአችንን እናቀርባለን።

ድል ለፋኖ
በክብር ለተሰው ሰማዕታት

ከዐማራ ማህበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ (ፋና)